# የሕዝቡ ቀጠኛ ተሳትፎ ወሳኝ ነው!!

## ለተግባራዊ ተሳትፎ መጠናከር አስቸኳይ ጥሪ

ሀገራችንን በሥልጣን ከባለጉት አጥፊዎችዋ መዳፍ ለማውጣት፣ የህዝቡን የሥልጣን ባለቤትነት ለማረጋገጥ፣ አንድነትዋንና ክብሯን ጠብቀን ለማቆየት፣ ሀገራዊ ሉዓላዊነትዋን ለማስመለስ፣ ዳር-ድንበርዋን ለማስከበር፣ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በማስፈንም የሕዝቡን ዘላቂ ጥቅሞች ለማረጋገጥ እንዲቻል ዛሬም በ'አንድነት ከመታገል ውጭ ሌላ መፍትሄ የለም እንላለን። ለዚህም፦
ከዚህ በፊት ባወጣናቸው ሁለት ተከታታይ የኅብትረት ጥሪዎቻችን መሠረት የሚፈለገውን ትልቅ ሀገራዊ ኅብረት ለመመሥረት አንድ ሁሉን-አቀፍ ጉባዔ ለመጥራት እነሆ የጉባዔ አዘጋጅ ኮሚቲ ለመስረት መመካከር ጀምረናል። ይህን አማራጭ የሌለውን ግዙፍ ሀገራዊ ዓላማ ለማሳካት የጉዳዩ ባለቤት፣ የሕዝቡ ተሳትፎ ወሳኝ ነውና ሁላችንም የዜግነት ሃላፊነታችንን ለመወጣት እንነሳ፣ በተናጠል የማይቻል ተግባርም ስለሆነ፣ እባካችሁ ሳንመናታ አብረን እናሳካው እንላለን።

በፖለቲካም ሆነ በሲቪክ ድርጅት መልክ የተሰባሰባችሁትንና በተለያዩ መንገዶች ጥሪአችን የደረሳችሁ፣ በተቃዋሚነት የህወሃት/ኢሕአዴግን መንግሥትና ሥርዓት እየተቃወማችሁ/ በመታገል ላይ ያላችሁትን ሃይሎች በሙሉ አሁንም ለሶስተኛ ጊዜ እባካችሁን አዎንታዊ ምላሻችሁን አትንፈጉን፤ የሁላችንም የጋራ የሆነችውን ሀገራችንን አሁን ከምትገኝበት አስከፊ ሁኔታ በ'አንድነት ታግለን እናውጣት ነው የምንለው። ከዚህ በፊት የተገናኟችሁን የ'እንቅስቃሴአችን ተወካዮች በመገናኘት፣ በስልክም ሆነ በኤለክትሮኒክ ሜይል ልትገናኙን ትችላላችሁ እንላለን።

ከዚህ ቀደም ዓላማችንን በመደገፍ አብራችሁን መሥራት የጀመራችሁትንና በተለያዩ የመገናኛ መንገዶች አብራችሁን ለመሥራት ቃል የገባችሁልንን ለቀና ምላሾቻችሁና ተሳትፏችሁ ከልብ እናመሰግናለን። ወደፊትም በርትተን እንድንቀጥል የሚያስፈልግ መሆኑን እየገልጥን፣ ትሥራችንን ለማጠናከርም ሆነ ተግባራዊ ተሳትፎአችንን መልክ ለማስያዝ በ'አካል መገናኘት ስለሚያስፈልግ የተወሰን አገናኞችን አድራሻ በመስጠት ረገድ ያላሟላችሁ ካላችሁ ትብብራችሁን እንጠይቃለን።

እስከዛሬ ድረስ ያልተሰባሰባችሁትን ሀገር-ወዳድ ኢትዮጵያውያን/ት በተመለከተ ግን፤ ሳንሰባሰብና ሳንደራጅ ትልቅ ሀገራዊ ቁምነገርን ለማሳካት ስለማኝጭል፣

1. ሕዝቡ በያለበት፣ የተወሰኑ ኢትዮጵያውያኑ በሚኖሩባቸው ከተሞች በሁሉም፣ የስብሰብ አስኳል መፍጠርና መንቀሳቀስ አለበት፣ ይሕ ደግሞ በግለሰቦች አነሳሽነት ሊጀመር ይችላል እንላለን
2. ሕዝቡ ዛሬ ራሱን የትግሉ ባለቤት፣ ነገ ደግሞ የሥልጣንም ባለቤት ሊያደርግ የሚችለው በራስ አነሳሽነት እየተሰባሰበ የፖለቲካ ሚና ለመጫወት ሲችል መሆኑን

ለአንዲት ደቂቃም ቢሆን መዘንጋት የለበትም፣ የሀገራችንን ጉዳይ በተመለከተ ሁላችንም ባለቤቶች ነን፣ ስለሆነም የተጀመረው የሀገራዊ ኅብረት ምሥረታ ሥራ የሁላችንም ነው

3. ማንኛውም የተወሰነ ቁጥር ያላቸውን ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን/ትን ያሰባሰበ አስኳል ከየትኛውም የሀገራችን ክፍል በጎቡዕ፣ ወይንም ከሀገር ውጭ ደግሞ በግልጽ ለኅብረት ምሥረታ እንቅስቃሴ ማድረግ የጀመረውን ቡድን በመገናኘት አብሮን ለመሥራት ይችላል። ዝግጁ ነንና ተገናኙን።

4. ከሀገር ውጭ የምትገኙና ገና በመሰባሰብ ላይ ያላችሁ ወይንም የተሰባሰባችሁ ወገኖቻችንን በተመለከተ እያደረግናቸው ባሉት ስብሰባዎቻችን ላይ ተወካይ/ዮችን በመላክ የተጀመረውን ዓላማ ለማሳካት አብረን እንድንሠራ አስቸኳይ ጥሪ እናቀርብላችኋለን።

5. የኢትዮጵያ ሕዝብ የወደፊት ዕድሉን፣ መብቱንና ጥቅሙን፣ የሀገሩንም ዕጣ በሙሉ ለተደራጁት የፖለቲካና የሲቪክ ሃይሎች ብቻ ሊተው አይገባውም። ሲሳቱና ሲያጠፉ መውቀስና ለማረም መጣር አለበት። እያወቁ የሚያጠፍ መሆናቸውን ሲያይ ደግሞ ሊያወግዛቸውም ይገባል። ሁኔታዎች ለመለወጥ ግን በቀጣይነት ሕዝቡ ራሱ ቀጥተኛ ሚናም ሊጫወት ይገባዋል። አርኪ ውጤትን ለማምጣት ግን መሰባሰብና መደራጀት እጅግ በጣም አስፈላጊ ነውና እንሰባሰብ፣ እንደራጅ እንላለን።

ለማስታወስ ያህል፦

ከዚህ በፊት ባወጣናቸው ሁለት ተከታታይ ጥሪዎቻችን ላይ የተገለጡት አራት ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው ፦

፩. በኢትዮጵያ አንድነትና የግዛት ሉዓላዊነት ላይ ግልጽና የማያወላውል ጽኑ እምነት መያዝና ማሳደር፣

፪. በየድርጅቶች ውስጥና በምንሰባሰብበት የኅብረት ማዕቀፍ ዉስጥ ዴሞክራሲያዊ አሰራርን ለማስፈንና በአገራችንም የሕግ የበላይነት እንዲኖር ጸንቶ መታገል፣

፫. በኢትዮጵያ ሕዝብ መካከል ምንም ዓይነት አድላዊነት እንዳይኖርና ሁሉም በሕግ ፊት እኩል ዜጎች መሆናቸዉን ማመንና በተግባርም ማስረገጥ፣

፬. የህወሓት/ኢህአዴግ መንግሥትና ሥርዓት የአፈናና የጭቆና ሥርዓት በመሆኑ መለወጥና በዴሞክራሲያዊ አስተዳደር መተካት እንዳለበት ማመን።

**አድራሻችን**
E-mail….   Consult4eth@gmail.com
Tel…..**ከአውሮፓ ሲደወል** 0039/329/7846516
**ከአሜሪካና ከካናዳ ሲደወል** 011/39/329/7846515
Webesite : http://www.derbiaber.com

አ ስ ተ ባ ባ ሪ ኮ ሚቴ ።

January, 2011